**- እውነት ብርቱ ተፋላሚ ነች፣ መዳረሻ ነች፤ አሸናፊ ነች -** ከበየነ

እጅግ ረዥም ዘመን ያስቆጠረችዋ ኢትዮጵያ የፍልሚያ፣ የድል፣ የአብሮነትና የአቃፊነት ታሪክ ነው ያላት። ኢ-ፍትሃዊነትን (injustice) ሲዋጉ የኖሩት ኢትዮጵያውያን መርሃቸው (Principle) ምንጊዜም እውነት (TRUTH) ነበረች። ኢትዮጵያውያን መልካም፣ ቅንና ፍርድ አዋቂ እንደነበሩ በቅዱሳን መጽሃፍትና በአዋቂዎች ተገልጸዋል። እስኪ ጥቂቱን እንኳን እንይ።

"ኢትዮጵያውያን እጅግ ሃቀኞች ናቸው" ሄሮዶቱስ – ግሪካዊ የታሪክ ምሁር «Ethiopians are the most just men» (Herodotus – Greek historian, 485-424 BC)
"ኢትዮጵያውያን እንከን የማይወጣላቸው ናቸው" ሆሜር – የግሪክ ጸሃፊ «Ethiopians are the blameless race» (Homer – Greek poet of the 8th century)
"የእስራኤል ልጆች ሆይ፣ እናንተ ለኔ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን? (አሞጽ9: 7)«Are you not like Ethiopians to me, O people of Israel? (Amos 9: 7)
ስህተት ፈጻሚዎች የማይገኙበት ሃገር፣ የጻድቃኖች ምድር" - ነብዩ ሙሃመድ «A country where no one is wronged; a land of righteosness (Prophet Muhammed)

እድላችንህ ሆኖ እኛ የደረስነው የማህበራዊ እድገት ነበራዊ ሁኔታዎች አዋቅረዋቸው የነበሩት የፖለቲካ አመለካከቶች ወይንም ርዕዮተ-ዓለሞች (Outlook – ideology) ሃይማኖቶች ሳይቀር እንዲናቁ እንዲጠወለጉ አልያም እንዲጠፉ በተፈለገበት ዓለም በምሥጢር በተሰባሰቡ ከበርቴዎች መዳፍ ሥር በወደቀችበት ዘመን ነው። የከበርቴዎቹ ድብቅ ማህበር የዓለምን ፖለቲካ የሚዘውረው ውሸት (falsehood)እና አስመሳይነት (pretentiousness) በማስማመርና በማደማመቅ ነው።

ውሸት በአመዛኙ የሚተገበረው በሃሰተኛ ፕሮፖጋንዳና በሥነ-ዓዕምሮ ጦርነት (psychological warfare)ሲሆን ከፍተኛ እገዛ የሚያደርጉለት ደግሞ ሃሳዊ መሲሆችና አሳሳቾች እንደ መተዳደርያ የሚገለገሉባቸው ማህበራዊ መገናኛዎች ናቸው። ዛሬ ላይ ሰዎች ለትልቅ ሥፍራ የሚታጩት ውሸታሞችና ዓይነ-ደረቆች መሆናቸው በቅጡ ተረጋግጦ ሲሆን ይልቁንም ተፅዕኖ ፈጣሪ፣ አንቱ ተብዬ፣ ዝነኛ፣ ተደናቂና ስኬታማ (influencers – high profile personalities – celebrities -impressive - successful) ከሆኑ ግለሰቦች መካከል እውነትን መጋረድ (eclipsing the Truth) የሚችሉት አስመሳዮች (imposters) በባትሪ ተፈልገው ለሹመት ይታጫሉ፣ ለሽልማት ይመረጣሉ።

ግሎባላይዜሽን የተባለው አዲሱ የምዕራቡ ዓለም ፖለቲካ ዝርፊያን የሚያበረታታ ብዙሃንን የሚያደኸይ ሥርዓት ነው። ጥቂቶች ለዘረፋ የሚያበቃቸውን የሥልጣን ጥማታቸውን ለማርካት በሚሄዱበት መንገድ ላይ በምስኪኖች ላይ ይራመዳሉ። ጥቅም ፈላጊዎች ገንዘብ ያጋበሱ እንጂ ተራሮች ቢናዱ ወንዞች ምድርን ቢያጥለቀልቁ ደንታም የላቸው። ይልቁንም የተጨነቁትን ሰብስበው "ተራሮች ሊናዱባችሁ ነው፣ ወንዙ ሊያጥለቀልቃችሁ ነው" በሚል አብዝተው ያስጨንቋቸዋል። እነሆ ሰዎች በፍርሃት ሲቁዘሙላቸው ደግሞ "የሚናዱትን ተራሮች አስቆምላችኋለሁ፣ ሊያጥለቀልቃችሁ የመጣውን ወንዝ አገድብላችኋለሁ" የሚል ሌላ ውሸት ፈጥረው ድሆችን ይበልጥ ያደኸያሉ፣ ያስርባሉ፣ ሰላማቸውን ሳይቀር ይነጡቋቸዋል።

ርዕዮተ-ዓለም ምናልባት አምባገነኖችን ሊጸንስ ይችላል። ውሸት ግን ጨካኝ ራስ ወዳዶችን ታብጃጃለች። የውሸታሞች ስብስብ ነው ዓለምን አጸያፊ ለማውራት እንኳን የሚዘገንን የኃጢዓት መከራ ያሸከማት። ግፈኞች በሠባዓዊ ጥበቃና ዴሞክራሲ ስም ኃጢዓትን ሕጋዊ እያደረጉ ነው። ውሸት መሳርያና መተግበርያ ነች። ሥልጣን ውሸት ነው። የትምህርት ደረጃ ውሸት ነው። ባለጸጋነት ውሸት ነው። ሌላው ቀርቶ የሠራዊትና የፖሊስ አደረጃጀት እንኳን ውሸታሞችን እንዲያገለግል ተደርጎ የተዋቀረ ነው። በጣም የሚገርመው ዘመኑ ትላልቅ የኃይማኖት መሪዎችን ሳይቀር ቀጣፊ አድርጓል።

በውሸታሞች መካከል የአመለካከት ልዩነት የለም። አብዛኞቹ ተንኮልን ተክነዋል። ከመካከላቸው አንዳንዶቹ የክፋት ባለ-ተሰጥዖ (evil genius) ወይንም የወንጀል አፍላቂዎች (criminal mastermind) ናቸው። ስብስባቸው አጭበርባሪና (humbug) አሳሳች (deceptive) ሰዎችን ያፈልቃል። ውሸት ማውራት (false talk) ማባዘን፣ ማጃጃል (trickery) የሙያ ያህል አድናቆት ይቸረዋል። አደነጋግሮ ማሳመን (making believe) ድብቅ ፍላጎትን

መተግበርያ ሆኗል። እውነት እና እውነታን (Truth and Reality) ያላዘለው ሃሳባቸው አያልቅም ምክንያቱም ከውሸት (falsehood) ባህር ነው የሚጨለፈው።

ኢትዮጵያውያን መልካም ማንነት እንደነበረን በጥቂቱም ቢሆን ከላይ ያሉትን አንብበን እንረዳለን። ኢ-ፍትሃዊነትን መታገል፣ ውሸትን መዋጋት የኢትዮጵያውያን የቆየ ኃይማኖት ነው። እምነታችን ከጨነገፈስ? የምናስበው ስለ ገቢያችን፣ ቤተሰቦቻችን ወይም የግል ጉዳያችን ብቻ ከሆነስ? በፍላጎቶች የታጠርን በምኞት ባርነት የምንሰቃይ ምንዱባን ከሆንስ – አኩሪ ታሪካችንን ማን ይጠብቃቸው፣ መልካም ማንነታችንን ማን ይመልሳቸው? የዘር ፖለቲካ አብሮነታችንን ካስተጓጎለስ? ጥቅም ለማግኘት ሲባል ውሸታሞቹን የሙጥኝ ካልንስ? እነሆ! ነፍሳችን ምን ይበጃት ይሆን?

ደሃው ዛሬ ላይ ሰላሙንና ጸጥታውን የሚያስጠብቅለት እረኛም መንግሥትም አጥቶ በጉልበተኞች እተተዘረፈ፣ እየታገተና እየተገደለ ሲባዝን ሳለ - ኑሮ አባክኖን፣ ድህነት ተጭኖን፣ ስደት አንገላቶን - እጆቻችንን በኅብረት ወደ እግዚአብሄር መዘርጋት ቢያቅተን እንኳን በራችንን ዘግተን ወደ ፈጣሪ ማንባት በተገባን ነበር። ሃገር እየሚሚች፣ እየተዋረደች ሳለ በየሚዲያው በሚቀርበውን የመዝናኛ ትዕይንት በመመልከት ራስን ማታለሉ ምን ሊፈይድ?

ሁሉን ብናወራው ብንዘከዝከው ሆድ ባዶ ይቀራል። በእምነትም ይሁን በሥራ፣ በንድፈሃሳብም ይሁን በተግባር ውሸትን መታገሉ ሥጋንም ነፍስንም ሃሴት ማልበስ ነው። ኢትዮጵያዊ ከኑሮውም ከትዳሩም በፊት ስለ አገሩ ይጨነቃል። ኢትዮጵያዊ ውሸትን ፈርቷት አይኖርም። ኢትዮጵያዊ አርቆ አልሞ ይራመዳል እንጂ ስሜት አይነዳውም። ሃሚታ፣ ቅናት፣ የሚተጋውን ማንቋሸሽ፣ ማጥላላት፣ አድፋጭነት - የኢትዮጵያዊ ጠባዮች አይደሉም። ዘመኑ የቱንም ያህል አስጨናቂ ይሁን ኢትዮጵያውያን ወደ ቀድሞው ማንነታችንን መመለስ አለብን። ኢትዮጵያውያን በኅልውና ለመኖርም ሆነ አኩሪ ታሪካችንን ለማስቀጠል መፍትሄው የተደበቀችብንን እውነት ፈልጎ አፈላልጎ ማግኘት ነው።

ኢትዮጵያዊ በጠንካራ ክንዱ የእውነትን ጠላቶች ሊደቁስ የተፈጠረ፣ የዓለም ሕዝብ በፍትህና በሠላም ይኖሩ ዘንድ መከራ የሚቀበል ዜጋ ነው። እምነት ሃቀኝነትና ፍትህ ወዳድነት የኢትዮጵያውያን ምልክቶች ናቸው። ኢትዮጵያዊ ቀንዲል ነው። ኢትዮጵያዊ - ታሪኩ፣ ወጉ፣ ትውፊቱ - እርሱ ተሰውቶ ለመላው የሰው ዘር ብርሃን መሆን ነው፣ አድዋም ምስክር ነች። እውነትን እግዚአብሄር ይወዳታል። ሃሰተኞች፣ ሃፍረተ-ቢሶች፣ የጨለማ ገዥዎች፣ ነዋይ አፍቃሪዎች፣ ርጎራሄ-ቢሶች - ያንገላትዋት እንደሆን እንጂ እውነት አትናወጥም። እውነት ብርቱ ተፋላሚ ነች፣ መዳረሻ ነች፣ አሸናፊ ነች።

"ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሄር ትዘረጋለች" መዝሙረ ዳዊት 67/68፣ 31